### ቍጥር ፳፪ ፲፱፻፴፬ ዓ. ም.

## በሕግ ፊት ባርነትና ሌሎችም አንዳንድ ነገሮች ፤ በፍጹም እንዲቀሩ የተደረገበት ፤ አ ዋ ጅ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ።
እኛ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

በንጉሠ ነገሥት ግዛታችን ውስጥ የባርነት ሁኔታ ፈጽሞ እንዲቀር የሁል ጊዜ ምኞታችንስለሆነ፤በ፲፱፻፲፮ ዓ. ም. መጋቢት ፳፪ ቀንና በ፲፱፻፳፫ ዓ. ም. ሐምሌ ፰ ቀን ነጻ ለመውጣት የፈለገ ባርያ ሁሉ ነጻነቱን በዳኛ ፊት እያረጋገጠ ነጻ ለመውጣት ይችላል ብለን አውጀን ስለነበረና እንዲሁም ቀጥለን ባርያ የሸጠና የገዛ ነጻነቱንም እንዳያገኝ የከለከለ ሰው ፤ የሚቀጣበትን ደንብ ወስነን ስለነበረ ፤ አሁንም ባርነት የሚባል ነገር በሕግ ፊት ከንጉሠ ነገሥት ግዛታችን ውስጥ ፈጽሞ እንዲጠፉ ፈቃዳችን ስለሆነ ፤ እንደሚከተለው አውጀናል ።

፩) ይህ አዋጅ በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም.ባርነትን ፈጽሞ ለማጥፋት የወጣ አዋጅ ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል ።

፪) በዚህ አዋጅ በቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው ካላስፈለገ በቀር ትርጓሜው እንደሚከተለው ነው ።

«ባርያ » ማለት ማናቸውም ሰው ሳይወድ በግድ በሌላ ሰው ታዛዥነት የሚኖር ማለት ነው ።

«ባርነት» ማለት አንድ ሰው ባንድ ሰው ላይ የባለቤትነትን መብት በግዴታ የሚያስፈጽምበት አኳኋን ማለት ነው ።

የባርያ ንግድ ማለት ፤ ማናቸውም ዓይነት የባርያ መፈንገል ፤ አንድ ሰው በባርነት እንዲገዛ ለማድረግ በገንዘብ መግዛት ወይም አስተላልፎ ለሰው መስጠት በማናቸውም ዓይነት ሰው መግዛት ፤ እንዲሸጥ ወይም እንዲለወጥ ፤ በመሸጥ ወይም በለውጥ ሰውን አሳልፎ መስጠት በጠቅላላው ማናቸውም ዓይነት በባርያ መነገድ ወይም ባርያ ካንድ ቦታ ወደ ሌላ እየወሰዱ ማቀባበል ይህን የመሰለው ሁሉ ከባርያ ንግድ ይቈጠራል ።

« በሕግ ፊት ያለው ሁኔታ » ማለት በሕግ የታወቀ አኳኋን ማለት ነው ።

፫) ባርነት የሚባል ነገር በሕግ ፊት ፈጽሞ የቀረ ሆኗል ።

፬) ማናቸውም ሰው አንዱን ሰው እንደባርያ እንዲሸጥ ከንጉሠ ነገሥት ግዛታችን የሚያስተላልፍ ፤ ወይም ለሚያስተላልፍ የረዳ ወይም በባርያ የሚነግድ ፤ ወይም በማናቸውም መንገድ በባርያ የሚነግደውን ማናቸውንም ሰው የረዳ ከወንጀለኛ ተቈጥሮ በጥፋቱ በተመሰከረበት ጊዜ እንደ ወንጀሉ ታይቶ ፤

(ሀ) በሞት ይቀጣል ።

ወይም ከ፳ ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከ፲ ሺ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከ፵ ጅራፍ በማይበልጥ ግርፋት ወይም ከነዚህ ከማናቸውም ቅጣቶች አጣምሮ ይቀጣል ።

፭) በዚህ አዋጅ መሠረት ማናቸውንም ባርያ ነጻነቱን እንዲያረጋግጥ የከለከለ ሰው ፤ ወይም ለመከልከል የሞከረ ፤ ወይም ባርያ ነህ ብሎ የያዘ፤ ወይም ለመያዝ የሞከረ፤ከጥፋተኛ ተቈጥሮ በጥፋቱ ሲመሰከርበት ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከአንድ ሺ ብር በማይበጥ መቀጮ ወይም አጣምሮ ይቀጣል ።

፮) ማናቸውም ሰው ሌላውን ሰው ለዕዳ መያዣ አድርጎ የሚያሳልፍና የሚቀበል ከጥፋተኛ ተቈጥሮ በጥፋቱ ሲመሰከር



No. 22 of 1942.

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ABOLITION OF THE LEGAL STATUS OF SLAVERY AND CERTAIN OTHER MATTERS

CONQUERING LION OF THE TRIBE OF JUDAH
HAILE SELASSIE I
ELECT OF GOD, EMPEROR OF ETHIOPIA

WHEREAS it has always been Our desire to abolish the institution of slavery in Our Empire;

AND WHEREAS by Our Proclamations of the 22nd. day of Megabit, 1916 and the 8th day of Hamlie, 1923, We proclaimed that all slaves who wished to be free could become free by asserting their freedom before a Judge;

AND WHEREAS We further provided for the punishment of persons who bought and sold slaves or who sought to prevent slaves from asserting their freedom;

NOW THEREFORE We desire to provide for the abolition of the legal status of slavery throughout Our Empire;

AND WE PROCLAIM AS FOLLOWS:—

1. This Proclamation may be cited as the Slavery (Abolition) Proclamation, 1942.

2. In this Proclamation, unless the context otherwise requires—

"slave" means a person whose condition is that of slavery;

"slavery" is the condition or status of a person over whom any or all the rights attaching to the right of ownership are exercised;

"Slave dealing" includes any act of capture, acquisition or delivery to another of a person with a view to reducing him to a state of slavery; any act of acquisition of a slave with a view to selling or exchanging him, any act of delivery to another by sale or exchange of a slave who was acquired with a view to being sold or exchanged, and generally any act of trading in or transporting slaves.

"legal status" means a status recognised by law.

3. The Legal status of slavery is abolished.

4. Any person who:—

(i) transports or assists in transporting a person out of Our Empire in order that he may be sold as a slave; or

(ii) engages in slave-dealing, or assists or in any way helps a person thus engaged;

is guilty of an offence and shall be liable on conviction,

(*a*) to be sentenced to death; or

(*b*) to imprisonment for a term not exceeding 20 years or to a fine not exceeding Maria Theresa dollars 10,000 or to corporal punishment not exceeding 40 lashes or to any combination of these penalties.

5. Any person who prevents or attempts to prevent any slave from asserting his freedom, or recaptures or attempts to recapture any slave who has asserted his freedom, shall be guilty or an offence and shall be liable on conviction to imprisonment for a period not exceeding 5 years or to a fine not exceeding Maria Theresa dollars 1,000 or to both such imprisonment and fine.

6. Any person who transfers or receives any other person as a pledge or security for a debt shall be guilty of an offence and shall be liable on conviction to imprisonment

በት ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም በሁለቱም አጣምሮ ይቀጣል ።

፯) በ፲፱፻፲፮ ዓ. ም. መጋቢት ፳፪ ቀንና በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም. ሐምሌ ፰ ቀን በታወጀው አዋጃችን ፈንታ ይህ አዋጅ ተተክቷል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳ ቀን ፲፱፻፴፬ ዓ. ም.

ጸ. ት. ወ. ጊዮርጊስ

የጽሕፈት ሚኒስትር ።

for a period not exceeding 2 years or to a fine not exceeding Maria Theresa dollars 500 or to both such imprisonment and fine.

7. The provisions of Our Proclamations of the 22nd. day of Megabit 1916 and the 8th. day of Hamlie 1923 are hereby re-enacted in so far as they are not inconsistent with the provisions of this Proclamation.

*Done at Addis Ababa this 26th day of August 1942.*

TSAHAFE TEZAZ WELDE GUIORGUIS

*Minister of the Pen*

Scanned by CamScanner